የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 26
ADDIS ABABA - 9th March, 2000


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፰/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የእንስሳት ፤ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ...............................ገጽ ፩ሺ፪፻፷፪


## CONTENTS


Proclamation No. 198/2000
Animal, Animal Products and By-products Marketing Development Authority Establishment (Amendment) Proclamation .................... Page 1262


### አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፰/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
### የእንስሳት ፤ እንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን ለማቋቋም የወጣው ማሻሻያ አዋጅ

የእንስሳት ፤ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የእንስሳት ፤ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፰/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

2· ማሻሻያ

የእንስሳት ፤ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፯/፲፱፻፺ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩· በአዋጁ ውስጥ "እንስሳት ፤ የእንስሳት ምርትና ተዋጽኦ ገበያ ልማት ባለሥልጣን" የሚለው ስያሜ "የእንስሳት ገበያ ባለሥልጣን" በሚል ተተክቷል ።

፪· አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል ፤

"፩· "እንስሳት" ማለት የዳልጋ ከብት ፤ በግ ፤ ፍየል ፤ ግመል ፤ ዶሮ ፤ አሣማ ፤ ንብ እንዲሁም ባለሥልጣኑ ወደፊት "እንስሳት" ብሎ የሚሰይማቸውንና ለዚህ አዋጅ ዓላማ ሲባል በአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) እንደተገለጸው የእንስሳት ምርትና የእንስሳት ተዋጽኦን ይጨምራል ።

### PROCLAMATION NO. 198/2000
### A PROCLAMATION TO AMEND THE ANIMAL, ANIMAL PRODUCTS, AND BY-PRODUCTS MARKETING DEVELOPMENT AUTHORITY ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the proclamation provided for the establishment of Animal, Animal products and By-products Marketing Development Authority;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Animal, Animal products, and By-Products Marketing Development Authority Establishment (Amendment) Proclamation No. 198/2000."

2. *Amendment*

The proclamation provided for the Animal, Animal Products and By-products Marketing Development Authority Establishment Proclamation No. 117/1998 is hereby amended as follows:

1) The "Animal, Animal Products and By-Products Marketing Development Authority," referred in the proclamation is replaced by and, shall be referred to as the "Livestock Marketing Authority."
2) Sub-Article (1) of Article 2 of the proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Sub-Article (1):
"1) "Livestock" means Cattle, Sheep, Goat, Camel, Poultry, Pig, Bee and which the Authority may designate as "Livestock", and for the purpose of this proclamation shall include livestock products and by-products as defined under Article 2 Sub-Articles (2) and (3) of the proclamation;"


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· በአዋጁ አንቀጽ ፲ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) ተጨምረዋል ፤

"፭ የባለሥልጣኑን ድርጅታዊ መዋቅርና የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል የባለሥልጣኑን ሙያተኛ ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል ፤ የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ በማውጣት ፤ መዋቅሩንና መመሪያውን ለመንግሥት በማቅረብ ያስጸድቃል ፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል ፤"

"፮· በሥራ አስኪያጁ የሚቀርበውን የመምሪያ ኃላፊዎችን ሹመትና ስንብት ያጸድቃል ።"

፬· የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፪/ለ/ ተተክቷል ፤

"ለ) ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሙያተኛ ሠራተኞች ይቀጥራል ፤ ያስተዳድራል ፤ ደመወዝና አበላቸውንም ይወስናል ፤ የባለሥልጣኑን ሌሎች ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል ፤ ያስተዳድራል ።

፫· *አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ*

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት



3) The following new Sub-Articles (5) and (6) are added under Article 10 of the proclamation.

"5) *following the basic principles of the federal* civil service laws, prepare and submit, to the government, the organizational structure and salary scale, a directive for the employment and administration of professional staff of the Authority, and follow up the implementation of same upon approval;"

"6) approve the appointment and dismissal of department heads proposed by the manager;"

4) Sub-Article 2(b) of Article 11 of the proclamation is hereby deleted and replaced by the following new Sub-Article 2(b):

"b) Employ and administer the Professional staff of the Authority in accordance with directive approved by the government and other staff in accordance with the federal civil service *laws;*"

3. *Effective Date*

This proclamation shall come into force as of the 9th day of March, 2000.

Done at Addis Ababa, this 9th day of March, 2000.

*NEGASO GIDADA (DR.)*

*PRESIDENT OF THE FEDERAL*

*DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

*ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ*

*BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE*